اللغة الأمهرية

በአማርኛ ቋንቋ

دليل المسلم الجديد، ما هو الإسلام؟

للشيخ د. هيثم سرحان

# የአዲሱ ሙስሊም መመሪያ

## ኢስላም ማለት ምን ማለትነው

Syaikh Dr. Haitsam Sarhan

# 3 የተዉሒድ ክፍሎች

ለእርሱ ለሌላ ለማንም የማይገቡ በጌትነቱ፣ በአምላክነቱና በስሞቹና ባህርያቱ አሏህን (عزوجل) መነጠል

በ3 ይከፈላል

### ተዉሒዱ አር-ሩቡቢያ (አሏህን በጌትነቱ መነጠል)

እሱም አሏህን (عزوجل) በተግባራቶቹ ወይም እርሱ ባስገኛቸዉ ነገራቶች፣ በበላይነቱና በማስተናበሩ መነጠል ነዉ

### ተዉሒዱ አል-ኡሉሒያ (አሏህን በአምልኮቱ መነጠል

እሱ አሏህን (عزوجل) በአምልኮ ወይም አምልኳዊ ድርጊቶች መነጠል ነዉ

### ተዉሒዱ አል-አስማኢ ወስ-ሲፋት (አሏህን በስሞቹና ባህሪያቱ መነጠል)

አሏህ (عزوجل) በኪታቡ ወይም በመልክተኛዉ እንደበት ራሱን በሰየመዉና በገለፀዉ እርሱን መነጠል ነዉ። ይህም እርሱን ለራሱ ያፀደቀዉን በማፅደቅ እና ከርሱ በጠረዉ ደግሞ በማጥራት ያለማንሻፈፍ፣ ያላማራቆት፣ እንዴትነትን ያለማድረግና ያለማመሳሰል ነዉ የሚሆነዉ።

# ሶስቱ የዲናችን እርከኖች

### አል እስላሙ

አሏህ ለርሱ ብቻ በመገዛት እጅ እግርን መስጠት፣ ለትዕዛዛቱ መንተትና ከጣዖት አምልኮትና ባለቤቶቿ መፅዳት ነዉ

የእስልምና መሰረቶች 5

1- ሁለተ ሸሃዳ
2- ሶላትን ማቆም
3- ዘካን መስጠት
4- ረመዷንን መፆም
5- ለቻለ ሰዉ ሀጅን ማድረግ

### አል-ኢማን

በምላስ የሚባል፣ በልብ የሚቋጠርና በአካላት የሚሰራ ሆኖ፣ ይጨምራል ይቀንሳልም

የኢማን ምሰሶዎች (መሰረቶች) 6

1- በአሏህ ማመን
2- በመላኢኮቹ ማመን
3- በመፅሃፍቶቹ ማመን
4- በመልዕክተኞቹ ማመን
5- በመጨረሻይቱ ቀን ማመን
6- በቀደር፣ ጥሩም ይሁን መጥፎዉ ማመን

### አል እህሳን

አሏህን እንደሚታያዉ ሆነህ ማምለክ ነዉ፣ አንተ ባታየዉም እርሱ ያየሃልና

አንድ መሰረት፣ ሁለት ደረጃዎች አሉት

1- ኢባደቱ አል-ሙሻህደ :- አሏህን እንደሚታየዉ ሆነ ማምለክ

2- ኢባደቱ አል-ሙራቀበ:- አንተ ባታየዉ እርሱ ያየሃል

# 4 የተከለከሉ ነገሪቶች ክፍሎች

### ትናንሽ ወንጀሎች

ከትላልቅ ወንጀሎች ዉጭ የሆኑ ናቸዉ። ትልቅ ወንጀሎች ንስህ በመግባት (ተዉባ በማድረግ/ ይማራሉ፣ ትናንሾቹ ግን ተጠራቅመዉ ትልቅ ይሆናሉ። ነብዩ ﷺ "ትናንሽ ወንጀሎችን ተጠንቀቋት፣ ሰሪዉ ግለሰብ ላይ ይጠረቃቀማሉ፣ እስኪያጠፉት ድረስ" አሉ።

### ትላልቅ ወንጀሎች

ያረሱ የሆነ ቅጣት የተደነገገለት ነዉ። ድግምት፣ ወላጆችን አለማክበር፣ ወለድ መብላት፣ ዝሙት፣ ግብረ ሰዶማዊነት፣ ዉሸት፣ አስካሪ መጠጥ፣ ሌብነት፣ ሀሜት፣ አሏህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለፍትህ መግደል ወዘተ ናቸዉ።

### ትንሹ ሽርክ

ከእስልምና አያስወጣም፣ ግን ከትላልቅ ወንጀሎች ትልቁ ነዉ። አሏህ ካለ እና አንተም ካልክ ማለትን ይመስል፣ ከአሏህ ዉጭ ባለን መማል፣ ይሉንታና፣ በገድ ማመን፣ ህርዝን ማንጠልጠል ወዘተ ከመጥፎ ነገር ወይም ከቡዳ ይከላከላሉ ብሎ ማድረግ ናቸዉ።

### ትልቁ ሽርክ

ከእስልምና ያወጣል። ስሞትም ምህረት አይጠየቅለትም። ልክ አሏህን እንደሚጣራ ሁሉ ብጤን አድርጎለት መጣራት፣ ወይም መፍራት ወይም መከጀል ወይም ለአሏህ ብቻ መሆን ያለበት አይነት ዉዴታን መዉደድ፣ አልያም ደግሞ ከኢባዳዎች አይነት የሆነን አሳልፎ መስጠት

الامهرية
አማርኛ

# 2 የውድዕ አደራረግ የተይሙምና የገላ አስተጣጠብ ሁኔታ

## የውድዕ አደራረግ

1 በልቡ ውዱዕ ለማድረግ ይነይታል ከዚያም እንዲህ ይላል : ቢስሚላህ በመቀጠል መዳፎችን ያጥባል



2 በቀኝ መዳፍ እጁ ውሃን በማድረግ (አፉን ይጉመጠመጣል ያመላልሠዋል);ከዚያም ይተፈዋል *ውሃ ይዞ ኢስቲንሻቅ ያደርጋል በአፋንጫው ይስበዋል*ከዚያም * በግራ እጁ አውራ ጣቱንና አመልካች ጣቱን አፋንጫውን በመያዝ የገባውን ውሃ ያስወጣዋል.



3 ከዚያም ፊቱን *በተለምዶ ከጭንቅላቱ የፀጉር ማብቀያ አንስቶ እስከ የፂም ማብቀያ መጨረሻ ድረስ አገጩን ጨምሮ ወደ ታች; ወደ ጉን ደግሞ ከጆሮ ጥግ እስከ ሌላኛው የጆሮ ጥግ ያጥበዋል*



4 ከዚያም እጆቹን ከጫፉ ጣቶቹ አንስቶ እስከ ክርኖቹ ቀኙን ቀጥሎ ግራውን ያጥባል.



5 ከዚያም ሙሉ በሙሉ የራሡን ፀጉር ያብሣል እጁን ከፊትለፊት ፀጉር አንስቶ ወደ ማጅራቱ ወስዶ ይመልስዋል.



6 አመልካች ጣቶቹን በጆሮ ውስጥ በማስገባት ያሻቸዋል በአውራ ጣቱም የላይኛውን የጆሮ ክፍል ያብሳል.



7 ከዚያም ቀኙን በማስቀደም ሁለት እግሮቹን እስከ ቁርጭምጭሚቱ ያጥባል.



8 -*ከተወሰነው የአስተጣጠበብ መጠነን መጨመር እንዴት ይታያል* በውድዕ ላይ ከተደነገገው ትጥበት መጨመር አይቻልም' ከሥስት በላይና ከእጆቹ ጡንቻዎች ከፍ አድርጉ ማጠብ መጨመርና የእግሩን ባት ከቁርጭሚት ከፍ አድርጉ ማጠብ አልያም ማጅራቱን ማበስ አይፈቀድም.



9 -ውድዑን ከጨረስ ቡሃላ የሚለው ድዓ:" አሽሃድአላኢላህ ኢለላህ ዋህደሁ ላሸሪከለሁ ; ወአሽሃድ አነ ሙሐመደን አብድሁ ወረሱሉሁ ".
በቲርሚዚ ዘገባ -" አላሁመ ኢጀአልኒ ሚነ ተዋቢን ወጅአልኒ ሚነ ሙተጣሂሪን ".

10 -ውድዕን የሚያጠፋ
1-ከሁለት ቀዳዳዎች የሚወጣው ሽንት አይነ ምድርና ፈስ.
2-ተይሙም ማለት : የውድዕ ምትክ ሲሆን ውሃን በስውነታችን ለመጠቀም ካልተቻለ ውሃን ባለማግኘት ወይም አደጋ ይደርስብኛል ብሎ ከስጋና ከፈራ ' ያን ጊዜ አፈርን እንደ ውሃ መጠቀም ይችላል
3-የግመል ሥጋ መብላት

## የተይሙም አደራረግ

1 ተየሙምን በቀልቡ ይነያና ከዚያም " ቢስሚላህ" ይበል ቀጥሎም መሬቱን ( አፈሩን ) በእጆቹ አንዴ መታ በማድረግ ፊቱን እና የእጆቹን መዳፎች የውጨኛ ክፍል ይበስ

2 ተየሙምን በቀልቡ ይነያና ከዚያም " ቢስሚላህ" ይበል ቀጥሎም መሬቱን ( አፈሩን ) በእጆቹ አንዴ መታ በማድረግ ፊቱን እና የእጆቹን መዳፎች የውጨኛ ክፍል ይበስ




3 -አፈሩን በምንመታበት ጊዜ- ጣቶችን መዘረጋትና በመሃከላቸው አፈሩን ማዳረስ ግድ አይሆንም.



## ግዴታዊ የገላ ትጥበት ሁኔታ

1 በልቡ መታጠብን ይነይታል በድብቅም (በዝቅተኛ ድምፅ) ቢስሚላህ ይላል ከዚያም ጠቅላላ ስውነቱን ውሃ ያዳርሣል ቀላልና ብዙ ፀጉር ያለበትን ክፍሎች በደንብ በውሃ ያስራጫል በመጉመጥመጥና በአፍንጫ ውሃን በመሣብ አዳርሶ ያጥባል.

2 መታጠብን ግዴታ የሚያደርጉ።
1. ጀናባ : ሚስትን መገናኘት የዘር ፈሣሽን ማፍስስ ይኖርበታል ወይም ብልትና ብልት መነካካት2-የወር አበባና የወሊድ ደም መፈስስ.
3-መስወዓት (ሽሒድ) ያልሆነ ሟች 4- ካፌር እስልምናን ሲቀበል ።

-አዘጋጅ :ዶ/ሐይስም ስርሐን ' በመስጂደ አነበዊ አስተማሪና "በሡና መአሃድ ሃላፊ:" http://mahadsunnah.com

# የነብያችን የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ 1

ኢማምና ተነጥሎ ለብቻው የሚሰግደው በሡትራ (በመከለያ) መስገድ ይኖርባቸዋል
የኢማሙ ሡትራ ለሱ ብቻ ሣይሆን ተከትለውት ለሚሰግዱትም መከለያ ይሆናል.

አይኑን ሡጁድ ከሚያርፋበት ቦታ ማይት ይኖርበታል.



1

የሁለት እግሮቹ የስፋት መጠን በትከሾቹ አቅጣጫ ልክ ያሰፋዋል ሣይጨምር ሣይቀንስ ተሰተካክሎ ይቆማል.



2

የስላት ቅድመ መስፈርቶችን ካሟላ ቡኋላ"አላሁ አክበር" በማለት እጆቹን በማንሣት በትከሻው ትክክል በማቅጣጨት ጣቶችን በማገጣጠም ተክቢራ ይላል .



3

የግራ እጁን መዳፍ ደረቱ ላይ የቀኝ እጁን ደግሞ የግራ መዳፉ ላይ ያደርጋል



4

ከዚያም በመጀመሪያው ረከዓ የመክፈቻ ዱዓ ቢያደርግ ይመረጣል "ሡብሃነከ ላሁመ ወቢሃምዲከ ወተባረከ ኢስሙከ ወተአላ ጀዱከ ወላኢላሃ ገይሩከ.
ከዚያም ከሸይጣን ይጠበቃል " አኡዙቢላሂ ሚነ ሸይጣኒ ረጂም ".
ከዚያም ቢስሚላህ ብሎ ፋቲሃን አስተካክሎ ተጂዊዷን ጠብቆ ረጋ እያለ ይቀራል (ያነባል).

بِسْمِ اللَّـهِ الرَّحْمَـٰنِ الرَّحِيمِ ﴿1﴾ الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ ﴿2﴾ الرَّحْمَـٰنِ الرَّحِيمِ ﴿3﴾ مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ ﴿4﴾ إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ ﴿5﴾ اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ ﴿6﴾ صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّالِّينَ (7)

-ከዚያም ከቁርአን አንቀፆች የገራለትን ይቀራል አኡዙቢላህ ባይል ይመረጣል ቢስሚላሂን በመጀመሪያ ሡራላይ ብቻ ያነባል.

5

ከዚያም እጁን በመጀመሪያው ረከዓ እንደነሣው " አላሁ አክበር"ይላል ከዚያም ሩኩዕ ያደርጋል ጉልበቱን በመያዝ ወገቡን ከጭንቅላቱ በማቅጣጨት ቀጥ ለጥ በማድረግ ተጉንብሶ አንድ ግዜ ብቻ በግዴታነት "ሡብሃነ ረቢየል አዚም ይላል" የሚያቃቸው ድዓዎች ካሉት ቢላቸው ይመረጣል.



6

ከዚያም ከሩኩዕ እየተነሣ ተስተካክሎ ሣይቆም እጁን በትከሻው ትክክል አቅጣጭቶ "ስሚአላሁ ሊመን ሐሚዳ " ይላል.

ተስተካክሎ ሲቆም ረበና ወለከል ሃምድ ይላል. የተገኙ ዱዓዎችን ቢጨምርበት ይመረጣል .

ከዚያም እጁን ሣያነሣ ወደ ስጁድ በሰባቱ የሠውነት ክፋሎች ይወርዳል: በግንባሩ; በአፋንጫው ; በውስጥ ሁለት መዳፋ እጆቹ ሁለት ጉልበቶቹ ;የሁለት የእግር የውስ ጣቶቹን ያካትታል.

-ብብቶቹንና ሆዱን እዲሁም ታፋዎቹን መዳፎቹንም ዘርዘር በማድረግ በስጁድ ጊዜ ክርኖቹን ከመሬት ያነሣቸዋል .

እንዲህም ይላል "ሡብሃነረቢየል አእላ " አንድ ጊዜ ግዴታ ሲሆን መጨመር ይችላል'የተመቸውን ሡናዊ በሆነ ዱዓ ያደርጋል.



7

ከዚያም ተክቢራ በማድረግ በግራ እግሩ ላይ እንደተዘረጋች ይቀመጥባታል የውስጥ ቀኝ አውራ ጣቱን መሬት ላይ ይለጥፋል



8

ከዚያም ተክቢራ በማድረግ የመጀመሪያ ስጁድ ይወርዳል ከዚያም ተክቢራ በማድረግ ለሁለተኛው ረከዓ በመነሣት በመጀመሪያ ረከዓ የስራውን ይደግመዋል ሁለተኛው ለየት የሚያደርገው ተክቢረተል ኢህራምና የመክፈቻ ድዓም አይደረግም.



9

ሁለተኛውን ሡጁድ ሲያጠናንቅ ለተሸሑድ ይቀመጣል.



ተስቢህ የሚያደርግባቸውን ጣቶቹን እያመላከተ አውራ ጣቱንና የመሐል ጣቱን በማገናኘት አመልካች ጣቱን እያንቀሣቀሰ የፈለገውን ዱዓ ያደርጋል .



ተሸውድ ከቀራ ቡኋላ የኢብራሂምያ ሰላዎት ያወርዳል "አታህያቱ ሊላሒ ' ወስለዎቱ ወጠይባቱ 'አስላሙአለይከ አዮሐል ነብዬ ወራህመቱላሒ ወበረካቱ 'አስላሙ አለይና ወአላ ኢባዲ ላሒ አሣሊሒነ አሽሐዱ አላ ኢላሐ ወአሽሐዱ አነ መሐመደን አብዱሁ ወረሡሉሁ 'አላሁመ ሠሌ አላሙሐመድን ወዓላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ሠለይተ አላ ኢብራሒመ ወአላ አሊ ኢብራሒመ ' ኢነከ ሐሚዱ መጂድ 'አላሁመ ባሪክ አላ ሙሐመዲን ወአላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ አላ ኢብራሒም ወአላ አሊ ኢብራሒም 'ኢነከ ሐሚዱን መጂድ.
ከዚያም ከአራት ነገር ይጠበቃል " አላሁመ ኢኒ አኡዙ ቢከ ሚን አዛቢ ጀሐነም 'ወአኡዙ ቢከ ሚን አዛቢ አልቀብር 'ወአኡዙ ቢከ ሚን ፊትነተ ደጃል 'ወአኡዙ ቢከ ሚን ፊትነተ መህያ ወልመማት ".የፈለገው ዱዓ ማድረግ ይችላል የሚበልጠው ሡናዊ በሆነ ዱዓ ቢለምን ይመረጣል ይሄንን ዱዓ ይጨምራል :" አላሁመ አኢኒ አላ ዚክሪከ ወሽኩሪከ ወሑስኒ ኢባደቲከ.
ከዚያም በቀኙና በግራው ካሠላመተ ቡሃላ እንዲህም ይላል" አስላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ " ትከሻውን ሣይሆን ጭንቅላቱን ብቻ ያዟዝሯል ወደ ፊት ለፊት ጉንበስ ቀና ባለማድረግ በመሐከላቸው በእጁም ሣይጦቅም ያጠናቅቃል.



10

አዘጋጅ : :ዶ/ሐይስም ስርሐን' በነብዮ መስጂድ አስተማሪና በመዓሐደ ሡና ሃላፊ ር/መምህር"mahadsunnah.com

ማተምና ማባዛት የተፈቀደ ነው - ፓንፖሌቶችን ለመቶርገም : sarhaan.com ወይም ፓርኮዱን ኮፒ ማድረግ

# ዘካ ለሁለት ይከፈላል፡-

1. ናፊላህ(ሱና የሆነ)፡-
የአላህ ፊት ተፈልጎበት የሚሰጥ ሶደቃ

2. ግዴታ የሆነ፡-
እሷም ደግሞ ለሁለት ትከፈላለች

## ዘካቱል በደን(ዘካተል ፊጥር) ፡-

ዘካተል ፊጥር በትልቅ በትንሽ ፤ በወንድ በሴት ፤ በባርያ በጨዋ በአጠቃላይ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ ነች

## የገንዘብ ዘካህ፡-

ዘካህ ሸሪዓ ባስቀመጠው ተመን(ሂሳብ) መሰረት ከሀብታሞች ተወስዳ ለድሆች የምትሰጥ የኢስላም ሶስተኛዋ ማእዘን(ሩክን) ስትሆን እሷም

ደግሞ ወደ አራት ትከፈላለች፡-

1 የወርቅ እና የብር ዘካ



ኒሷባቸው ደግሞ ለወርቅ 85ግራም ሲሆን ለብር ደግሞ 595ግራም ነው። አንድ ሰው ከነዚህ አንዱ ከደረሰ ወይንም ይህንን ያህል ግራም የሚያስገዛ ብር ካለው ዘካ ይወጅብበታል ማለት ነው።

2 የእንስሳት ዘካ



አንድ ሰው ያለው የእንስሳት ቁጥር ሸሪዓው ለዘካ ያስቀመጠው ልክ ላይ ከደረሰ ዘካ ይወጅብበታል። ዘካ የሚወጣባቸው እንስሳቶች፡- ግመል ፤ ከብት ፤ ፍየል እና በግ ናቸው።

3 ከመሬት የሚበቅሉ ነገራቶች



ዘካ እነሱም፡- አዝርእት እና የፍራፍሬ ናቸው።

4 ለግብይት



(ለሽያጭ የተዘጋጁ ነገራቶች)

## ዘካ የሚሰጣቸው ሰዎች፡-

1 ድሆች፡- ምንም ለሌላቸው ድሆች ወይንም ያላቸው ነገር የማያብቃቃቸው ለሆኑ ድሆች

2 ሚስኪኖች፡- ከድሆች ትንሽ ሻል ያሉ ነገር ግን ያላቸው ገንዘብ ጉዳዮቻቸውን ለማስፈፀም የማይሞላላቸው ደሀዎች

3 ለዘካ ሰራተኞች፡- የዘካ ሰራተኞች ስንል የሚፈለግበት ሰብሳቢዎቿ፣ ጠባቂዎቿ እና አከፋፋይ ወኪሎቿ ናቸው። የዘካ ሰራተኞች ዘካ ለመቀበል የግድ ድሀ ካልሆኑ አይባልም ሀብታም ቢሆኑ እንኳን ሰራተኛ እስከሆኑ ድረስ ዘካ ይሰጣቸዋል። የሚሾማቸውም የሀገሩ አስተዳዳሪ መንግስት ነው።

4 ልባቸው (ከኢስላም) የሚላመድ፡- ይሰልማሉ ተብለው ተስፋ የሚጣልባቸው ወይንም ከሸራቸው ለመገላገል(ለመጠበቅ) እና የመሳሰሉት ናቸው።

5 ሪቃብ (ለጫንቃ ባለቤቶች) እነሱም፡-
ሀ, ከባርነት ነፃ ለመሆን የተዋዋለ
ለ, ሙስሊም ባርያን ነፃ ለማውጣት
ሐ, ሙስሊም ምርኮኛ

6 ባለ እዳዎች፡- እነሱም፡-
ሀ በሰዎች መካከል ለማስታረቅ እዳ የገባ
ለ, እዳ ያለበት ሰው

7 በአላህ መንገድ ላይ ለሚታገሉ፡- ለነሱ ቀለብ እንዲሆናቸው ወይንም ለትጥቅ መግዣ ይሰጣቸዋል።

8 ለመንገደኛ፡- መንገድ ላይ ስንቁ ያለቀበት ሃገሩ የሚያደርሰውን ያክል ይሰጠዋል።

አማርኛ أمهرية

# ፆም ሁለት አይነት ነው

ዋጂብ የሆኑ፡ የረመዷን ፆም፣ የከፋራህ ፆም እና የስለት ፆም ናቸው

ነፍል(ሱና የሆኑ)፡ ከነዚህ ውጭ ያሉት ናቸው

**የ ፆም ማብራሪያ፡** ፆም ብሎ ማለት ትክክለኛው ፈጅር ከወጣበት ሰአት ጀምሮ ፀሃይ እስከምትጠልቅበት ሰአት ድረስ ከምግብ ፣ ከመጠጥ እንዲሁም ከማንኛውም የሚያስፈጥሩ ነገራቶች እራሳችንን በመቆጠብ አላህን የምንገዛበት የ ዒባዳ አይነት ነው።

## ለፆም ሁለት ማእዘናቶች አሉት

### 1 ኒያህ

| የግዴታ ፆም ኒያህ፡ | የነዋፊል(የሱና) ፆም ኒያህ፡ |
|---|---|
| ለግዴታ ፆም ኒያውን ማሳደር አለበት(ማለትም ከፈጂር በፊት ቀኑን በፆም እንደሚያሳልፍ መወሰን መነየት አለበት) ለእያንዳንዱ ቀን ራሱን የቻለ ኒያህ ያስፈልገዋል። የኒያ ቦታዋ ደግሞ ቀልብ ነው። በምላስ ድምፅን አውጥቶ ማለት ቢድዓ ነው። | የሚያስፈጥር ነገር እስካልፈፀመ ድረስ በማንኛውም የቀኑ ክፍል መነየት ይችላል። ነገር ግን አጅሩ የሚታሰብለት ኒያ ካደረገበት ሰአት ጀምሮ ነው። |

### 2 ከሚያስፈጥሩ ነገራቶች መታቀብ



### ፆምን የሚያበላሹ ነገራቶች፡

1 አውቆ መብላትና መጠጣት፣ ረስቶ ከሆነ ግን ፆሙ አይበላሽም።
2 ፆታዊ ግኙነት ማድረግ፣ይህንን የፈፀመው በረመዷን ቀን ላይ ከሆነ ከባድ የሆነ ከፋራ(ማሳበሻ) ያስፈልገዋል
3 መንይን ማፍሰስ
4 ምግብን የሚተኩ ነገራቶችን መጠቀም ለምሳሌ የምግብ መርፌ(ግሉኮዝ)
5 በዋግምት ደምን ማውጣት
6 አውቆ ማስታወክ
7 የወሊድ ደም እና የወር አበባ ደም መፍሰስ

### ለፆመኛ ከሚፈቀዱ ነገራቶች

- ለሐጃ ምግብ መቅመስ
- ምራቅን መዋጥ
- ሻወር መውሰድ
- ሲዋክ መጠቀም
- ሽቶ መቀባት
- ራስን ማቀዝቀዝ

## የፆም መስፈርቶች

| | |
|---|---|
| 1- ኢስላም | 2- አእምሮ ጤነኛ መሆን |
| 3- ለአቅመ አዳም መድረስ፣ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ህፃናቶች እንዲፆሙ ሊበረታቱ ይገባል። | |
| 4- ቋሚ ኗሪ መሆን፣ ለመንገደኛ ፆም መፆም ግድ አይሆንበትም፣ ፆሙ የማይጎዳው ከሆነ ግን በጉዞ ላይ መፆሙ የተሻለ ነው። | |
| 5- ጤነኛ መሆን | 6- ከወር አበባና ከወሊድ ደም ንፁህ መሆን |

### በፆመኛ ላይ ሐራም የሆኑ ነገራቶች

1 አክታን መዋጥ
2 ባለቤቱን መሳም፡ ፆሙን እንደማይፈታ እርግጠኛ ላልሆነ ሰው
3 ቀውለዙር (ሃራም የሆኑ ነገራቶችን መፈፀም) 4 ጀህል(ቂላቂልነት)
5 ፆምን ሳያፈጥሩ ለተከታታይ ቀናት መፆም
6 በዋግምት ደምን ማስወጣት 7 አውቆ ማስታወክ

### ለፆመኛ የሚጠሉ ነገሮች

1 ድንበር ያለፈ ባፍንጫ ውሃ መሳብና መጉመጥመጥ
2 ያለምንም ሐጃ ምግብን መቅመስ



የሐጅ አፈጻፀም በአጭሩ
አማርኛ
أمهرية
هيئة سرحان
የሻም እና የግብጽ ሰዎች ሚቃት አል ጁህፋ 186 km
የመዲና ሰዎች ሚቃት ዙል ሑሌይፋ 420 km
የኢራቅ ሰዎች ሚቃት ዛቱ ዒርቅ 98 km
የነጅድ ሰዎች ቀርነል መናዚል 99 km
የየመን ሰዎች ሚቃት የለምለም 99 km
1
ኢሕራም
ወደ ሐጅ ለመግባት ኒያ ማድረግ
በአውሮፕላን የሚሄዱ ሰዎች በሚቃት ሰማይ ላይ ሲያልፉ ቅርብ ቦታው ላይ ኢህራም ያደርጋሉ
2
የመጀመሪያ ጠዋፍ
ከጥቁሩ ድንጋይ (ሐጀረል አስወድ) እስከ ሐጀረል አስወድ 7 ዙር መዞር
መጀመሪያ
መጨረሻ
ከአረንጓዴ ምልክቶች በፊትና በኋላ ረጋ ብለህ ትሄዳለህ በአረንጓዴ ምልክቶች መካከል በመሮጥ ማለፍ ለወንዶችም ብቻ ነው።
መርዋ
ሰፋ
3
በሰፋ እና በመርዋ መካከል መጓዝ
ዘጠኛ ቀን
5
በአረፋ መቆም
9ኛ ቀን ዙህር ጀምሮ እስከ 10ኛ ቀን ፈጅር በሷ ውስጥ ዙህር እና አስር ጀምዑ ተቅዲም አድርጎ የሰግዳል
ለ9ኛ ቀን ለሊት
4
ሚና መደር
8ኛ ቀን ዙህር፣ አስር፣ መግሪብ እና ኢሻዕ ሰላቶችን እና የ9ኛ ቀን ፈጅር ሰላትን እዚያው ይሰግዳል
ለ10ኛ ቀን ለሊት
6
ሙዝደሊፋ ማደር
አንድ ላይ አድርጎ እና አሳጥሮ መግሪብ እና ኢሻዕን በ9ኛ ቀን ይሰግዳል የ10ኛ ቀን ፈጅርንም
9
ለ10 ቀን ለሊት
መላጨት ወይም ማሳጠር
መላጨት ወይም ማሳጠር ለወንዶች ሲሆን ለሴቶች የጣት አንጓ የምታክል ነው
ለ10 ቀን ለሊት
7
ትልቁን ጀምረተል አቀባ በ 7 ጠጠር ይወረውራል
ትንሿን ጉርጓድ ከዚያም መካከለኛዋን እና ትልቁን ከዙህር በኋላ መወርወር
8
ለ10 ቀን ለሊት
ሐድይ ማረድ ለሙተመቲዕ እና ለቃሪን
ጀምራ ጠጠር መወርወር እንዲሁም ሚና ማደር
ጉርጓድ 3
ጉርጓድ 2
ጉርጓድ 1
የዱዓ ቦታ
የዱዓ ቦታ
12
11ኛ 12ኛ እና 13ኛን ለሚቆይም
13
የመሰናበቻ ጠዋፍ
ለ10 ቀን ለሊት
ጠዋፈል ኢፋዳ
10
ለሙተመቲዕ ሰፋ መርዋ ሰዕይ ማድረግ ወይም የመጀመሪያ ጠዋፍ ላይ ሰእይ ላላደረገ ሰው
11
ወር አበባ ላይ እና የወሊድ ደም ላይ ላሉት ይተዋል
• የሐጅ ምሰሶዎች (አርካኖች)፡ አንድን ሩክን የተወ ሰው እሷን እስካልተገበረ ሐጁ ምሉእ አይሆንም
• የሐጅ ግዴታዎች፡ አንድን የሐጅ ዋጂብ የተወ ሰው በእርድ ይተካዋል
alsarhaan.com
sarhaan.com

# የዑምራ ስነ-ስርአት

አማርኛ أمهرية

## 1 ኢሕራም

ወደ ስነ-ስርአቱ መግቢያ ኒያ

- የሻምና የግብፅ ሰዎች ሚቃት ጁሕፋህ 186ኪ.ሜ
- የመዲና ሰዎች ሚቃት ዙል ሑለይፋህ 420ኪ.ሜ
- የዒራቅ ሰዎች ሚቃት ዛቱ ዒርቅ 98ኪ.ሜ
- የነጅድ ሰዎች ሚቃት ቀርኑል መናዚል 99ኪ.ሜ
- የየመን ሰዎች ሚቃት የለምለም 99ኪ.ሜ

በአውሮፕላን የሚመጡ ሰዎች በሚቀርባቸው ሚቃት ሰማይ ላይ ሲበሩ እዛው ፕሌን ወስጥ ሆነው ኢሕራም ያደርጋሉ

## 2 ጠዋፍ ማድረግ

ከሓጀረል አስወድ እስከ ሓጀረል አስወድ ሰባት ዙር መዞር

መጀመሪያ | መጨረሻ

## 3 ከመቃሙል ኢብራሂም ኋላ መስገድ(ከተቻለ)

## 4 በሰፋ እና በመርዋ መካከል መጓዝ

### ሰባት ዙር

ሁለቱ አረንጓዴ ምልክቶች እስኪትደርስ ድረስ ትራመዳለህ አረንጓዴው ምልክት ጋር ስትደርስ እስከዛኛው አረንጓዴ ምልክትድረስ በፍጥነት በሰፋ እና መርዋ መካከል ትሮጣለህ ይህ ተግባር ለወንዶች ብቻ ነው።

ሶፍስ

መርዋ

## 5 መላጩት ወይንም ማሳጠር

መላጩት ወይንም ማሳጠር ለወንዶች ሲሆን ለሴቶች ደግሞ የጣታቸውን ጫፍ ያክል ማሳጠር

## ኢሕራም ላይ የተከለከሉ ነግራቶች

1. ፀጉርን ከራስም ሆነ ከሰውነት ማስወገድ
2. ጥፍርን መቁረጥ
3. ሽቶ መጠቀም
4. ለራሱም ሆነ ለሌላ ሰው ኒካህ ማሰር
5. ሴትን መገናኘት
6. የየብስ እንሳቶችን ማደን

### ለወንዶች ብቻ የተከለከሉ

1. በሰውነት ቅርፅ የተሰፉ ልብሶች፣ባጠቃላይ ማንኛውም የተሰፋ ልብስ
2. ራስን በጥምጣም ሆነ በኮፍያ መሸፈን

### ለሴቶች ብቻ የተከለከሉ

1. ፊትን በኒቃብ ወይንም በቡርቁዕ መሸፈን የተከለከለ ነው። ነገር ግን በአከባቢዋ አጅነቢ ወንዶች ካሉ በሻሽ ነገር ፊቷን ትሸፍናለች
2. ጓንት መልበስ

## ለዑምራ የሚወደዱ ተግባሮች

1. የኢሕራም ኒያ ከማድረጋችን በፊት ጥፍርን እንዲሁም አላስፈላጊ ፀጉሮችን ማስወገድ
2. ለኢሕራም ሻወር መውሰድ
3. ሰውነትን በሽቶ ማሳመር (ለወንዶች ብቻ)
4. ነጭ ጋቢና ሽርጥ ማሸረጥ
5. ተልቢያ(ለበይለኳሁመ ለበይክ...)ከኢሕራም ቦታችን እስከ ጠዋፍ
6. የቀኝ ትከሻውን ክፍት ማድረግ
7. ሓጀረል አስወድን መሳም
8. የመጀመሪያ ሰወስት ዙሮችን ፈጠን ፈጠን እያሉ መራመድ
9. ከመቃሙል ኢብራሂም ኋላ ሁለት ረከዓ መስገድ




# ነብዩ ሙሀመድ (ሰ. አ. ወ.) ማናቸው ?ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን?

ዶ/ሼኽ ሀይስም ሰርሐድ የቀድሞ የመስጂዶ አነበውይ አስተማሪና በመአሃድ አሱና ሐላፊ የሆኑት መምህር ትንታኔና ማብራሪያ ስጠውበታል፡፡

ባርኮዱን እንዲያነብ አድርገው - sarhaan.com

## ነብዩ ሙሀመድ (ሰ. ኣ. ወ.) ማናቸው ? ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን ?

- እሳቸው የሰዎችን መብት እንዳይጣስ በመከላከል ከ 1400 ኣመት በፊት ዘብ የቆሙ ናቸው !

- ወንዶችን ሴቶችን ህፃናትን ደካሞችን ሁሉ ጠብቀዋል!

- የእንስሳዎችንና የእፅዋት መብትና ሃቅ በመንከባከብ ደንበር

- በጎረቤት እና በዝምድና መካከል ጥሩየሆነ ግንኙነት ስነምግባር እንዲኖር ኣዘዋል!

- በሙስሊሞች እና ሙስሊም ባልሆኑ መሀከል ያለውን

- ነብዩ ሙሀመድ (ሰ.ኣ. ወ.)የቤተሰብግንኙነት የእናትና ኣባት ሀቅ በልጆች ላይ ያለውን ከባድ መሆኑን ኣደራ ጥለዋል!

## ነብዩ ሙሀመድ (ሰ. ዐ. ወ.) ማናቸው ? ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን ?

- በደልን ማስወገድ እና ወደ ፍትሀዊነት መተሳሰርን በጥሩ ነገር መተባበርን አረጋግጠዋል!

- ለችግረኞች እርዳታ ማረግ የታመመን መጠየቅ በሰዎች መሀል መልካም ንግግር መነጋገር አስተምረዋል!

- ሙስሊሞችን ከመጥፎ ስነ ምግባር ከልክለዋል በደልን

- መጥፎን ባህሪ ወደ መልካም ባህሪ ቀይረዋል

- ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን እንዳይሰርቅ አዘዋል!

- ሙስሊሞችን እንዳይዋሹ አስተምረዋል!

- ሙስሊሞች አስካሪ መጠጥ እንዳይጠጡ አስተምረዋል!

## ነብዩ መሀመድ (ሰ. ኣ. ወ.) ማናቸው?
## ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን?

- ኣንድ ሙስሊም ዝሙት እንዳይሰራ ከልክለዋል !

- ሙስሊሞቹን እንዳያታልሉ ኣዘዋል!

- ሙስሊሞችን በጦርነት ሜዳ ላይ ለጦርነት ያልመጡ ሰዎችን እንዳይገሉ ከልክለዋል

- ሙስሊሞች ጎረቤቶቻቸውን ሙስሊም ይሁን ካፊር

- ሙስሊሞች ለወላጆቻቸው መልካም ነገር እንዲውሉላቸው በሌላ እምነት ላይ ቢሆኑ እንኩዋን ብለው ኣዘዋል!

- ሙስሊም የሆነ ሰው በህፃናት በሴቶች ወይም በደካሞች ላይ እንዲያዝኑ ኣዘዋል! ሀቁንእንዳይዳፈሩ ኣዘዋል!

- ኣንድ ሙስሊም በእንስሶችና በእፅዋት ላይ ድንበር እንዳያልፍ ኣዘዋል!

## ነብዩ ሙሀመድ (ሰ. ዐ. ወ.) ማናቸው ? ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን ?

- ነብዩ(ሰ. ዐ. ወ.)ያስተማሩት ለሰው እንዲያዝን እና እንዲታዘንለት ሚስቱንም እንዲወድ እና እንዲከባከብ በልጆቹዋ

- በልጆቹ መሀል እና በሱ መካከል ለአቅመ አዳም ቢደርሱም እንኳን ከልጆቹ መለየት እንዳሌለበት አስተምረዋል !

- ሁሉም ሙስሊም ነብያችንን (ሰ. ዐ. ወ.) ከሁሉም ፍጥረት አብልጦ መውደድ አለበት!

- ሙሳም ኢሳም በነብያችን ላይ (ሰ. ዐ. ወ.)መምጣት አበስረውን አልፈዋል።

- ሁሉም ሙስሊም በሙሳ በኢሳ (ዐ. ሰ.)በነሱም ያምናል ከተከበሩት አምቢያወች መሆናቸውን ያምናል።

- ነብዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ. ወ.) አረብ ለሆኑትም ላልሆኑትም ሰዎች ተልከዋል።

## ነብዩ ሙሀመድ (ሰ. ኣ. ወ.) ማናቸው ?
## ስለሳቸውስ ምን እናውቃለን ?

- በዲን ላይ ለኣረብም ለሌሎችም ምንም ኣይነት ልዩነት የለም ኣላህን በመፍራት ካልሆነ በስተቀር።

- ነብዩ ሙሀመድ (ሰ ኣ የኣላህ መልዕክተኛ ናቸው!

- ኣወቃችሁን ሁሉም ሰው ሙስሊም የሆነ ነብዩ ሙሐመድን(ሰ.ኣ. ወ.) ለምን እንደሚወድ?

- ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ኣ. ወ.)ለሙስሊሞች ምን ማለት እንደሆኑ ኣሁን ተረዳችሁ?

ከፌስቡክ ድህረ ገጻችንን ጎብኙን።

የሼክ ድህረገጸ መኣሃድ ኣሡና

sarhaan.com

ዓመት ተቋም

mahadsunnah.com